የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ ዓመት ቁጥር ፲፱
አዲስ አበባ የካቲት ፲ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

20th Year No. 19
ADDIS ABABA 17th February 2014

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፰፻፳፭/፪ሺ፮ ዓ.ም

የሕፃናት ሽያጭን፣ የሕፃናት የወሲብ ንግድና የሕፃናት የወሲብ ቀስቃሽ ፊልሞችን ለመከላከል የወጣው የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ተጨማሪ ፕሮቶኮል ማጽደቂያ አዋጅ……………………………………………ገጽ ፯ሺ፪፻፶፫

CONTENTS

Proclamation No. 825/2014

Optional Protocol to the Convention on the Rights of the Child on the Sale of Children, Child Prostitution and Child Pornography Ratification Proclamation … ……………………………… Page 7253

## አዋጅ ቁጥር ፰፻፳፭/፪ሺ፮

## የሕፃናት ሽያጭን፣ የሕፃናት የወሲብ ንግድና የሕፃናት የወሲብ ቀስቃሽ ፊልሞችን ለመከላከል የወጣውን የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ተጨማሪ ፕሮቶኮል ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

የሕፃናት ሽያጭን፣ የሕፃናት የወሲብ ንግድና የሕፃናት የወሲብ ቀስቃሽ ፊልሞችን ለመከላከል የወጣውን የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ተጨማሪ ፕሮቶኮል እ.ኤ.አ ሜይ ፳፭ ቀን ፪ሺ በኒውዮርክ በተካሄደው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሃምሳ አራተኛ ጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ የወጣ በመሆኑ፤

ይህንኑ ፕሮቶኮል የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፳ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የሕፃናት ሽያጭን፣ የሕፃናት የወሲብ ንግድና የሕፃናት የወሲብ ቀስቃሽ ፊልሞችን ለመከላከል የወጣው የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ተጨማሪ ፕሮቶኮል ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፳፭/፪ሺ፮" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PROCLAMATION No. 825/2014.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE OPTIONAL PROTOCOL TO THE CONVENTION ON THE RIGHTS OF THE CHILD ON THE SALE OF CHILDREN, CHILD PROSTITUTION AND CHILD PORNOGRAPHY

WHEREAS, the Optional Protocol to the Convention on the Rights of the Child on the Sale of Children, Child Prostitution and Child Pornography has been adopted on the 25th day of May, 2000 at the fifty-fourth session of the United Nations General Assembly held in New York;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Protocol at its session held on the 28th day of January, 2014;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Optional Protocol to the Convention on the Rights of the Child on the Sale of Children, Child Prostitution and Child Pornography Ratification Proclamation No. 825/2014".

| ያንዱ ዋጋ<br>Unit Price | 2:30 |
| --- | --- |

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ ፹ሺ፩
Negarit Gazette P.O.box 80,001

፪. **<u>የፕሮቶኮሉ መፅደቅ</u>**

እ.አ.አ. ሜይ ፳፭ ቀን ፪ሺ. በኒውዮርክ በተካሄደው የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ሃምሳ አራተኛ ጠቅላላ ጉባዔ የወጣው የሕፃናት ሽያጭ፣ የሕፃናት የወሲብ ንግድና የሕፃናት የወሲብ ቀስቃሽ ፊልሞችን ለመከላከል የወጣው የሕፃናት መብቶች ኮንቬንሽን ተጨማሪ ፕሮቶኮል በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

፫. **<u>የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ፕሮቶኮሉን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ እርምጃዎችን የመውሰድ ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

፬. **<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት ፲ ቀን ፪ሺ፮ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

2. **<u>Ratification of the Protocol</u>**

The Optional Protocol to the Convention on the Rights of the Child on the Sale of Children, Child Prostitution and Child Pornography, adopted on the 25th day of May 2000, at the fifty-fourth session of the United Nations General Assembly, held in New York, is hereby ratified.

3. **<u>Power of the Ministry of Women, Children and Youth Affairs</u>**

The Ministry of Women, Children and Youth Affairs is hereby empowered to undertake all acts necessary for the implementation of the Protocol.

4. **<u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 17th day of February, 2014**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**